አማራ ባንክ

AMHARA BANK

ከባንክ ባሻገር

Beyond Financing!

# ዓመታዊ ሪፖርት
# ፳፻፲፫/፲፬

አማራ ባንክ
AMHARA BANK
ከባንክ ባሻገር
Beyond Financing!

## ርዕይ

በአፍሪካ ቀዳሚ እና ጨዋታ ቀያሪ ባንክ መሆን።

## ተልዕኮ

በብቁ እና በስነምግባር በታነጹ ሠራተኞች ዓለም የደረሰበትን ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም መጠነ ሰፊ፣ ተደራሽ፣ አስተማማኝ እንዲሁም ፈጠራ አዘል በሆነ መልኩ ደንበኛን ትኩረት ያደረጉ የፋይናንስም ሆነ ሌሎች አገልግሎቶችን ማኅበራዊ ኃላፊነትን ተላብሶ መስጠት ነው።

## ቁልፍ እሴቶች

- ፈጠራ እና አካታች
- ማኅበረሰብ እና ደንበኛ ተኮር
- ተጠያቂነት እና ተደራሽነት
- ኃላፊነት የሚሰማው እና አክብሮትን የተላበሰ
- ብቃት እና ውጤታማነት

ማውጫ


የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ መልዕክት....2

የዋና ሥራ አስፈፃሚ መልዕክት....5

የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት....8

የውጭ ኦዲተሮች ሪፖርት....15

የትርፍ ወይም ኪሳራ መግለጫ....18

የሀብት እና ዕዳ መግለጫ....19

የካፒታል መግለጫ....20

የጥሬ ገንዘብ ፍሰት መግለጫ....21

# የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ መልእክት



ውድ ባለአክሲዮኖች፣ የመጀመሪያ የሆነውን ታሪካዊ የአማራ ባንክ የ 2021/22 እ.ኤ.አ የሂሳብ ዓመት ሪፖርት ሳቀርብ የተሰማኝን ታላቅ ደስታ በራሴ እና በባልደረቦቼ በዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ስም ለመግለጽ እወዳለሁ። ባንኩ ዛሬ ለቆመበት ጠንካራ መሠረት ባደረገው አስደናቂ ጉዞ ውስጥ ሂደቱን ለመምራትና ለመደገፍ እድል በማግኘቴ ታላቅ ኩራት ይሰማኛል።

ባንኩን በከፍተኛ ስኬት አገልግሎት ማስጀመር በመቻላችን፣ ለሁላችንም ዓመቱ ትልቅ ስኬት የተመዘገበበት ነበር። ባንኩን ለመመስረት የተደራጁ ቡድኖች፣ ባለአክሲዮኖች፣ አደራጅ ኮሚቴና ሠራተኞች ባደረጉት የተቀናጀ ጥረት በርካታ ፈተናዎችን ተቋቁመው ጽናታቸውን ባያሳዩና ከአሠራሩ ጋር በተጣጣመ መልኩ እና ለወደፊቱ ጠንካራ መሰረትን ለመጣል ከቁጥጥር ደንቦች አንፃር ባይሠሩ ኖሮ ድሉ ሊሳካ አይችልም ነበር። ከሁሉም በላይ ከኅብረተሰቡ የተሰጠን ጠንካራ ሕዝባዊ ተቀባይነት እና ያልተቋረጠ ድጋፍ በዋናነት እ.ኤ.አ. ሰኔ 18 ቀን 2022 አማራ ባንክን ወደ ኢንዱስትሪው ለማስገባት ለተደረገው ጥረት ጥንካሬና ብርቱ የመንፈስ ድጋፍ ሆኖናል።

በዓመቱ ውስጥ ሀገሪቱ ከሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎች የሚመነጩ ሁለገብ ችግሮች ተጋርጠውባት ነበር። በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የተራዘመው ጦርነት እና በበርካታ አካባቢዎች ፖለቲካዊ አለመረጋጋት ያስከተለው ተጽእኖ፣ በአንዳንድ ቦታዎች የኢኮኖሚ እንቅስቃሴን በማወኩ ምክንያት የተፈጠረው የዋጋ ንረትና የጥሬ እቃ አቅርቦት ችግር ዋነኛ ፈተናዎች ነበሩ። በተጨማሪም በሩሲያ እና በዩክሬን መካከል በተፈጠረው ጦርነት ምክንያት የተከሰተው ዓለም ዓቀፍ ከፍተኛ የዋጋ ንረትና የሀይል አቅርቦት ቀውስ

ችግሩ ይበልጥ እንዲባባስ ምክንያት ሆኗል። እነዚህና ከሌሎች ከውጭና ከባንክ ኢንዱስትሪው የሚመነጩ ተግዳሮቶች ቢኖሩም መንግሥት የወሰዳቸው የፖሊሲ እና አስተዳደራዊ ውሳኔዎችና የተለያዩ ጥልቅ ተሃድሶዎች በአገር አቀፍ እንዲሁም በባንክ እንዱስትሪ ደረጃ በዓመቱ ለተመዘገበው እድገት ጉልህ አስተዋጽዖ ነበራቸው።

ነገር ግን በእነዚህ ዓመታት ውስጥ በሕብረት እንደ አንድ የአማራ ባንክ ቤተሰብ በጋራ በቁርጠኝነት በመቆማችን ያጋጠሙንን ተግዳሮቶች በመጋፈጥ፤ ሀብትን ለማደራጀት፤ አቅም ለመመስረትና ስልታዊ በሆነ መንገድ ለመጓዝ ከፍተኛ ጥንካሬ ሆኖናል። ደንበኞቻችንን የጥረታችን ማዕከል ባደረገ መልኩ፤ በዓመቱ የተለያዩ የደንበኛ ፍላጎቶችን በተሻለ ሁኔታ ለማሟላት፤ ይበልጥ ሳቢ እሴቶችን ለመፍጠር፣ ለተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች አገልግሎት ለመስጠት፣ በቅልጥፍና፣ በፈጠራ እና በትብብር መርሆዎች ላይ የተመሰረቱ አዳዲስ የሥራ መንገዶችን በማጎልበት፤ የተለያዩ ዋና ዋና ሥራዎችን በማከናወን፤ ተደራሽነትን በማስፋት ገበያን ማሳደግ እና ከፍተኛ ልምድ ያለው የሰው ኃይል ለመገንባት ርብርብ ተደርጓል።

ከላይ ከተጠቀሱት ተግባራት ጎን ለጎን ከባለአክሲዮኖቻችን እና ከኅብረተሰቡ የተደረገልን ድጋፍ በዋነኛነት የ 2021/22 እ.ኤ.አ የበጀት ዓመት ከማለቁ በፊት ባንኩ ሥራውን እንዲጀምር ከፍተኛ ጉልበት ሆኖናል። ባንኩ ለሕዝብ በሩን እንደከፈተ በሁሉም ቅርንጫፎቻችን ሒሳብ ለመክፈት የተሰለፉው የደንበኞች ጎርፍ ባንኩ ከኅብረተሰቡ ከፍተኛ ተቀባይነት እንዳለው በተግባር የታየበት ነው። ይህም በበጀት ዓመቱ በጥቂት የሥራ ቀናት ውስጥ ብቻ በ1,425 ብቁ እና ተነሳሽነት ባላቸው ሠራተኞች ድጋፍ ከሰማኒያ ሁለት ሺህ በላይ ደንበኞችን እንድናገኝና ብር 401.1 ሚሊዮን ቁጠባ ለማሰባሰብ አግዞናል። እንዲሁም፤ እ.ኤ.አ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2022 ድረስ ብቻ 75 ቅርንጫፎችን ወደ ሥራ ከማስገባቱም በተጨማሪ ስምንት የኤቲኤም ማሽኖች በአዲስ አበባ እና በባሕር ዳር በመተከላቸው ባንኩ በዲጂታል መንገድ ተደራሽ ለማድረግ ያለውን ቁርጠኝነት በተግባር አሳይቷል። በዋናዋና ከፋይናንስ አፈጻጸም አመላካቾች አንጻር ሲታይ፤ ባንኩ አጠቃላይ ገቢ 531 ሚሊዮን ብር የሰበሰበ ሲሆን ለዚህም በዋናነት ባንኩ አክሲዮን በመሸጥ የሰበሰበው የአገልግሎት ክፍያ ጉልህ ድርሻ አበርክቷል። በአጠቃላይ ለሥራ ማስኬጃ ብር 294 ሚሊዮን ወጪ በማድረጉ ከታክስ በፊት እ.ኤ.አ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2022 ድረስ ብር 237 ሚሊዮን ትርፍ አስመዝግቧል። በተጨማሪም ባንኩ የብር 4.8 ቢሊየን የተከፈለ ካፒታል በማስመዝገብ ጠንካራ ካፒታል ለማሰባሰብ የተደረገው ጥረት ውጤታማ ነበር ማለት ይቻላል። የባንኩን መመሥረቻ ሰነድ ያልፈረሙት ቀሪ ባለአክሲዮኖች እንዲፈርሙ ቢፈቀድ ኖሮ ደግሞ፤ የተከፈለው የካፒታል መጠን ከዚህ ሊበልጥ ይችል ነበር።

ምንም እንኳን ይህ ጉባዔ እ.ኤ.አ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2022 ድረስ ያለውን አፈጻጸም ለመገምገም ቢሆንም ባንካችን በተገለጸው ጊዜ ለ11ቀናት ብቻ በመሥራቱ ሙሉ አፈጻጸም ለማየት ስለማያስችል፤ ይህ ጉባዔ መረጃ እንዲኖረው ባንካችን እ.ኤ.አ እስከ ህዳር 30 ቀን 2022 ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ 178 ቅርንጫፎችን በመክፈት 476,288 ደንበኛ ማሰባሰብ ያቻለ ሲሆን ብር 7.5 ቢሊዮን ተቀማጭ ገንዘብ በማሰባሰብ ብር 4.8 ቢሊዮን ብድር ሰጥቷል።

በቀጣይነትም፤ ደንበኞቻችን ከእኛ ጋር እንዲሠሩ በተግባር ከታየው ፍላጎት አንጻር እና ከሁሉም በላይ ደግሞ ባንኩ በግልጽ ደንበኞችን ያማከለ አገልግሎት ለመስጠት ካለው ፍላጎት አንፃር የተለያዩ ምርቶችን እና አገልግሎቶችን በመንደፍ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍል ፍላጎቶችን የሚያሟሉ የላቀ የደንበኞች አገልግሎት ለማቅረብ በቁርጠኝነት እንሠራለን።

በተጨማሪም ከደንበኞች ጋር ቀጣይነት ያለው ግንኙነት ለመመሥረት እና አዳዲሶችን ለመሳብ ባንኩ በቅርንጫፍና እና በዲጂታል አገልግሎት መስጫ መንገዶችን በመጠቀም የብዝሃ አገልግሎት መስጫ መንገዶችን የመተግበር ስትራቴጂያችንን አጠንክረን እንቀጥላለን። "የጨዋታ ቀያሪ ባንክ" የመሆን ርዕያችንን ለማሳካት ልህቀትን፣ ፈጠራን እና ሥራችንን ዲጂታል ለማድረግ ሰፋ ያለ ትኩረት እንሰጣለን። ስለዚህ ባንኩ የቀን ተቀን የደምበኞች አገልግሎትን በቴክኖሎጂ የተደገፈ ከማድረግ ባሻገር የተለያዩ ዘመናዊ የዲጂታል አገልግሎቶችን ማለትም ሞባይል ባንኪንግ፣ ኢንተርኔት ባንኪንግ፣ ኤጀንሲ ባንኪንግ፣ ዲጂታል ብራንች፣ አይቲኤም እና ሞባይል ብራንች ወደ አገልግሎት ለማስገባት ከፍተኛ ርብርብ እየተደረገ ነው።

በተጨማሪም፣ ከባንክ ባሻገር አገልግሎት የመስጠት መርሐችን በዕለት ተዕለት ተግባራችን ውስጥ በሚገባ

የተካተተ መሆኑን እናረጋግጣለን፣ ስለዚህም የደንበኞችን ፍላጎት በግለሰብና በአነስተኛና መካከለኛ ደረጃ ላይ ያሉ ተቋማትን ለመደገፍ የበለጠ እንሠራለን።

በተጨማሪም የሚኒስትሮች ምክር ቤት በፋይናንሺያል ዘርፍ የውጭ ኢንቨስትመንትን መፍቀዱን ተከትሎ ታይቶ የማይታወቅ የባንክ ኢንዱስትሪ ገጽታ ለውጥና፤ በፋይናንሺያል አገልግሎት አሰጣጥ ላይ እንደ ቴሌኮም እና ፊን-ቴክ ያሉ የገንዘብ ነክ ያልሆኑ አገልግሎት ሰጪዎች ተሳትፎ፤ ሁለቱንም እድሎች እና ፈተናዎች ያመጣል። ከዚህም አንጻር ባንኮች ስጋቶቻቸውን ለመቀነስ የተለያዩ እርምጃዎችን እየወሰዱ ይገኛሉ። ከነዚህ እርምጃዎች ውስጥ አንዱ የካፒታላቸውን መጠን ማሳደግ ይገኝበታል።

ባንካችን ምንም እንኳን በከፍተኛ የተፈረመና የተከፈለ ካፒታል መጠን ዘርፉን ቢቀላቀልም፤ ከነባር ባንኮች የካፒታል ምጣኔና፤ ከሚመጣው ውድድር አንጻር አሁን ያለው የካፒታል መጠን በቂ እንዳልሆነ መገንዘብ አያዳግትም። ስለሆነም ይህ ጉባኤ፤ ያልተከፈለው የአክሲዮን ድርሻ በጊዜው ገቢ እንዲሆን አጽንኦት የሚሰጥበትና፤ በተጨማሪም፤ ባንካችን ሁነኛ ተወዳዳሪ ብሎም አሸናፊ ሆኖ እንዲቀጥል የባንኩ ካፒታል መጠን እንዲያድግ እንዲሁም ለውህደት ወይም ለመግዛት የቅድመ ሁኔታ ሥራዎች እንዲሠሩ አቅጣጫ ያስቀምጣል ተብሎ ይጠበቃል።

ይህ ስኬት እንዲቀጥል ለማድረግ ሌላ ደማቅ አሻራ የማሳረፍ የቤት ሥራ ከፊታችን ይጠብቀናል። ከራሳችሁ ጀምሮ፤ ቤተሰቦቻችሁ፣ ወዳጅ ዘመዶቻችሁ፣ ባለሃብቶች፣ ተቋማት፣ ልዩ ልዩ ማኅበራት፤ የባንኩ አጋሮችና ደጋፊዎች፤ ወዘተ ገንዘባቸውን በባንካችን እንዲያስቀምጡና ከባንካችን ጋር እንዲሠሩ የማድረግ ማለትም የባንኩ አምባሳደርና የሕዝብ ግንኙነት በመሆን ታላቅ ኀላፊነታችሁን እንድትወጡ መልእክት ሳስተላልፍ ከዚህ በላይ በመሥራት ስኬታማነታችንን በተግባር እንደምታስመሰክሩ በመተማመን ነው።

በመሆኑም ባንኩ በእንደስትሪው ያለውን ተለዋዋጭ ሁኔታ በንቃት በመከታተል ተገቢውን ስትራቴጂ በመንደፍ ፈጣን ምላሽ በመስጠት ይተጋል። ለዚህም ባንኩ የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ እቅዱን እና የአስር ዓመት ትግበራ ፍኖተ ካርታን ለመሥራት ዓለም አቀፍ አማካሪዎችን በመቅጠር ከውስጥ አቻ ቡድን ጋር በመተባበር የእውቀት ሽግግርን እና እንከን የለሽ ትግበራዎችን በማሳለጥ ዝግጅት ላይ ነው። እየተለወጠ ለሚመጣው የባንክ ኢንዱስትሪ ምላሽ ለመስጠት የባንኩን ካፒታል በማሳደግ ከነባር እና ከውጭ ከሚመጡ የውጭ ተወዳዳሪዎች ጋር በብቃት ለመወዳደር ጥረት ያደርጋል። አጋሮችን ለመሳብ እንዲሁም ውህደትን አላማ በማድረግ አስቦ እየሠራ ነው። ከዚህ አንጻር ከሚታሰቡ ጉዳዮች አንጻር የካፒታል ማሳደግ አንዱ ነው። ይህ ጉባኤ የባንኩን ካፒታል ለማሳደግ በቀረበው ምክረ ሃሳብ ላይ ተወያይቶ እንዲያጸድቅ ይጠበቃል።

በመጨረሻም የተከበራችሁ ደንበኞቻችን ላሳያችሁን እምነት እና በራስ መተማመን ከልብ አድናቆቴን መግለጽ እወዳለሁ። እናም ፍላጎታቸውን ለማሳካት አብረናቸው እንደምንቀጥል ላረጋግጥላቸው እወዳለሁ። በተመሳሳይ ባንኩን ወደ ሥራ ለማስገባት ላደረጉት ቁርጠኝነት እና ያላሰለሰ ጥረት የባንኩን አመራሮች እና ትጉህ ሠራተኞቻችንን ከልብ አመሰግናለሁ። በተጨማሪም በሁሉም ረገድ ላደረጋችሁት የማይናወጥ እምነትና ድጋፍ ለባለአክሲዮኖቻችን ያለኝን ጥልቅ አድናቆትና ምስጋና በዚህ አጋጣሚ መግለጽ እፈልጋለሁ። እንዲሁም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለሰጠን መመሪያና ድጋፍ ለማመስገን እወዳለሁ።

*መላኩ ፈንታ*
*ቦርድ ሰብሳቢ*

# የዋና ሥራ አስፈፃሚ መልእክት



የአማራ ባንክ አ.ማ. ዓመታዊ የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ ለ1ኛ ጠቅላላ እና ድንገተኛ የባለአክሲዮኖች ጉባኤ እንደ መስራች ዋና ሥራ አስፈፃሚ መልዕክት ማስተላለፍ በመቻሌ ኩራት ይሰማኛል። በተጨማሪም ለባንኩ ጠንካራ መሰረት ለመጣል እና በዚህ ተነሳሽነት ላይ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ ያፈሰሱ ሰዎችን ህልም እውን ለማድረግ አደራ ስለተሰጠኝ ከፍተኛ ደስታ ይሰማኛል። ይህ ውጤት የተገኘው በአደራጅ ኮሚቴው፣ በዳይሬክተሮች ቦርድ እና በሠራተኞች በተቀናጀ ጥረት እና ቁርጠኝነት እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል።

እንደሚታወቀው አማራ ባንክ ሥራውን የጀመረው ሀገራችን ከውስጥም ሆነ ከዓለም አቀፋዊ ጉዳዮች የሚመነጩ በርካታ ፈተናዎች ውስጥ በነበረችበት ወቅት ነው። በወቅቱ በኮቪድ-19 የተፈጠረውን ተግዳሮት በመቋቋም ላይ የነበረው የዓለም ኢኮኖሚ ሌሎች አዳዲስ ፈተናዎች ገጥመውት ነበር፤ እንደ አብነትም፤ የሩሲያ-ዩክሬን ጦርነት በመከሰቱ ምክንያት ከኮቪድ ወረርሽኝ እያገገመ የነበረው ኢኮኖሚ እንዲያሽቆለቁል ምክንያት ሆኗል፣ የአቅርቦት ሰንሰለትን በማስተጓጎል፣ በተለይም የምርት እንቅስቃሴ በማዛባት እና የዋጋ ግሽበት በመጨመር የማክሮ ኢኮኖሚው እንዳይረጋጋ ተጽዕኖ አድርሷል። በሀገር ውስጥ ደግሞ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በዓመቱ በተፈጠሩ ችግሮች ምክንያት ተደራራቢ ተጽዕኖዎች ደርሶበታል። በተለይም በሰሜናዊው የሀገራችን ክፍል በተከሰተው ጦርነት እና በሌሎች አካባቢዎች በተከሰቱ ግጭቶች የተራዘመው የፖለቲካ ግጭት ጦርነቱ በተከሰተባቸው አካባቢዎች ያለውን ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ እንዳይኖር ወይም

እንዲቀዛቀዝ እና የሀገራችን ኢኮኖሚያዉ ዕድገት በተፈለገው መልኩ እንዳይሄድ አድርጓል። ነገር ግን ከተከሰቱት መጥፎ ዕድሎች በተቃራኒ ሀገራችን በጠንካራ ሁኔታ እና አዎንታዊ እድገት በማስመዝገብ ከሚጠበቀው በላይ ሆና ቆይታለች። በተመሳሳይ ከላይ የተጠቀሱ ተግዳሮቶች ቢኖሩም የባንክ ኢንዱስትሪው በአብዛኛዎቹ ቁልፍ የአፈጻጸም አመልካቾች ላይ ጠንካራ ውጤቶችን አስመዝግቧል።

ባንኩ በተቋቋመበት የመጀመሪያ ዓመት የሁሉም ባለድርሻ አካላት ዋና ትኩረት ባንኩን ውጤታማ በሆነ መንገድ ማስጀመር እና ለደንበኞቹ ጥራት ያለው አገልግሎት እንዲሰጥ የሚያስችለውን ብቃት ማሳደግ ነበር። በተጨባጭም ሁሉንም ሀብቶቻችን እና ችሎታዎቻችን በማጣመር መፈፀም በምንፈልጋቸው ስትራቴጅዎቻችን ላይ ትኩረት አድርገናል። ይህም ዘላቂ የመፈፀም አቅማችንን ለመገንባትና ለሁሉም ባለድርሻዎች ዘለቄታዊ እሴት እንድንፈጥር ያስችለናል። በመጨረሻም በዝግጅት ምዕራፍ ያከናወናቸው ጥረቶች ፍሬ አፍርተው የአማራ ባንክ እ.ኤ.አ. ሰኔ 18 ቀን 2022 በዋናው መሥሪያ ቤት በደማቅ የመክፈቻ ሥነ-ሥርዓት ወደ ኢንደስትሪው በመቀላቀል ውጤታማ እንዲሆን አድርጎታል። ባንኩ በመጀመሪያው ቀን 72 ቅርንጫፎችን መክፈቱም ከዚህ ቀደም ታይቶ የማይታወቅ ሲሆን ይህም በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ወደ 75 ቅርንጫፎች ከፍ ብሏል። በዕለቱም ባንካችን በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ለሚገኙ ነዋሪዎች በሙሉ የአንበሳ የከተማ አውቶብስ ትኬቶችን ዋጋ በመክፈል ሁሉም ማኅበረሰብ በነፃ አገልግሎት እንዲያገኝ በማድረግ፣ በአገሪቱ በተመረጡ ሆስፒታሎች ለተወለዱ ህጻናት ስጦታ በመስጠት፣ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን ሕይወት ለመታደግ ደም በመለገስ እና በሠራተኞች ችግኝ በመትከል ማኅበረሰባዊ ኃላፊነቶችን የተወጣ ሲሆን በተለያዩ አካባቢዎች በከፈታቸው ቅርንጫፎች በመጠቀም በርካታ ተግባራትን በማከናወን ተከብሯል።

ባንካችን የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ባደረጉት ርብርብ የባንኩን አሠራር ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገርና በዚህም ምክንያት ደንበኞቻችንና አጠቃላይ ኅብረተሰቡ የሚጠብቀውን በማሟላት ባንኩ ሥራ በጀመረበት የመጀመሪያው በጀት ዓመት (2021/2022) አበረታች ውጤት አስመዝግቧል። በዚህም መሰረት ባንኩ በሪፖርት ዘመኑ በ75 ቅርንጫፎቹ ከ82 ሺህ በላይ አስቀማጮችን በመሳብ ብር 401.1 ሚሊዮን ተቀማጭ ሰብስቧል፤ እንዲሁም ጎን ለጎን ባንኩ ብር 531 ሚሊዮን ገቢ የሰበሰበ ሲሆን ብር 294 ሚሊዮን አውጥቶ 237 ሚሊዮን ብር ከታክስ በፊት ትርፍ አስመዝግቧል። ይህም በአክሲዮን ካፒታል ሽያጭ ወቅት የተሰበሰበውን የአክሲዮን የአገልግሎት ክፍያ መዋጮ መሰረት ያደረገ ነው። በሌላ በኩል ባንኩ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ ስምንት የኤቲኤም ማሽኖችን በአዲስ አበባና በባሕር ዳር ከተሞች ከኢት-ስዊች የክፍያ ሥርዓት ጋር በማቀናጀት በዲጂታል ባንክ አገልግሎት መስጠት መጀመሩ ያስቀመጠውን ውጥን ለመፈፀም ያለውን ቁርጠኛነቱን አሳይቷል።

ባንኩ እንደ አንድ አስፈላጊ ግብ "ከባንክ ባሻገር" ከሚለው ፍልስፍና ጎን ለጎን "በአፍሪካ ግንባር ቀደም እና ጨዋታ ቀያሪ ባንክ" የመሆን ርዕዩን የበለጠ አካታች ለማድረግ ቁርጠኞች ነን። ይህንንም እውን ለማድረግ በልማት ፋይናንስ በሥራ ክፍላችን አማካኝነት የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ፍላጎት ይበልጥ በተጠናከረ መልኩ ለማገዝ አስፈላጊውን ሁሉ እናደርጋለን። ከዚህ በተጨማሪም ባንኩ አሠራሩን ዘመናዊ ለማድረግ እና ብቃቱን ለማሳደግ የተለያዩ የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን ወደ ትግበራ ማስገባቱን በመቀጠል በሞባይል፣ በኢንተርኔት፣ በኤጀንሲ ባንኪንግ፣ በኤቲኤም፣ በፖስ ማሽኖች በመጠቀም የቴክኖሎጂ እውቀት ያላቸው እና የተማሩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ተደራሽ ለማድረግ ከዲጂታል አገልግሎት በተጨማሪ የዲጂታል ቅርንጫፎች በመጠቀም ከሌሎች የዲጂታል ክፍያ ስርዓትን ከሚያመቻቹ

ድርጅቶች ጋር በመጣመር የበለጠ ተደራሽነትን ለማጎልበት ይሠራል።

በተጨማሪም የሚኒስትሮች ምክር ቤት በፋይናንስ ዘርፍ የውጭ ኢንቨስትመንት መፍቀዱን ተከትሎ በፋይናንሺያል አገልግሎት አሰጣጥ ላይ እንደ ቴሌኮም እና ፊን-ቴክ ያሉ የገንዘብ ነክ ያልሆኑ አገልግሎት ሰጪዎች ተሳትፎ ሁለቱንም መልካም እድሎችና ፈተናዎች ያመጣል። በመሆኑም ባንኩ በኢንዱስትሪው ያለውን ተለዋዋጭ ሁኔታ በንቃት በመከታተል ተገቢውን ስትራቴጂ በመከተል ምላሽ መስጠት ይኖርበታል። ለዚህም ባንኩ የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ እቅዱን እና የአስር ዓመት ትግበራ ፍኖተ ካርታን ለመሥራት ዓለም አቀፍ አማካሪዎችን በመቅጠር፣ ከውስጥ አቻ ቡድን ጋር በመተባበር የእውቀት ሽግግርን እና የማያቋርጥ ትግበራን ለማካሄድ በዝግጅት ላይ ይገኛል።

በእኛ ባንክ ለመገልገል ለመረጣችሁ እና ጠንካራ መሰረት ለመጣል በምናደርገው ጉዞ ብርታታችን ለሆናችሁ ውድ ደንበኞቻችን ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። በተመሳሳይ ሠራተኞቻችን ባንኩ ዓላማውን እንዲያሳካ ላደረጉት ከፍተኛ ጥረት እና የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ፣ የፋይናንሺያል ኢንተለጀንስ ማዕከል እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ላደረጉልን ክትትልና ድጋፍ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። ከዚህም በተጨማሪ ለፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት እና አስተባባሪ ኮሚቴ ቡድኖች ባንኩ በተሳካ ሁኔታ ወደ ሥራ እንዲገባ ላደረጋችሁት አስደናቂ ጥረት እና ቁርጠኝነት እንዲሁም የዳይሬክተሮች ቦርድ ባንኩን በማደራጀት፣ ግብዓቶችን እና ጊዜን በማቀናጀት ረገድ ላደረጋችሁት ጠቃሚ ድጋፍ፣ ትጋት እና መመሪያ አድናቆቴን መግለጽ እፈልጋለሁ።

በመጨረሻም የተከበራችሁ ባለአክሲዮኖች ከጎናችን በመሆን ለምታደርጉልን ድጋፍ እያመሰገንሁ እና ከባንካችን ጋር እንድትሠሩ እየጠቅሁ፤ በአመራርና በሠራተኞቻችን ትጋት ሁሉንም ባለድርሻ አካላት በማርካት ከርዕያችን ከፍታ ላይ ደርሰን ከምንጠብቀው በላይ እንደምናሳካ እርግጠኛ ነኝ።



*ሄኖክ ከበደ*
*የዋና ሥራ አስፈፃሚ*

# የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት

*የአማራ ባንክ የዳይሬክተሮች ቦርድ በቁልፍ የባንክ ሥራዎች የተመዘገቡትን ዋና ዋና ተግባራት እና እ.ኤ.አ ሰኔ 30 ቀን 2022 ለተጠናቀቀው በጀት ዓመት የኦዲተር ሪፖርት ለባለድርሻ አካላት ሲያቀርብ በደስታ ነው።*

## 1. ዋና ዋና የቅድመ ጅማሮ-ሥራዎች

እኤአ በታኅሳስ 2021 ባንካችን የምሥረታ ጉባዔውን ከአካሄደ እና የኘሮጀክት ሥራውን ካጠናቀቀ በኃላ ከተወሰኑ የከፍተኛ ሥራ አመራር እና ቦርድ አባላት ጋር በመሆን ሥራው ሲሠራ ቆይቷል። በመቀጠልም የባንኩ ማኔጅመንትና ሌሎች ሠራተኞች በቦርድ አባላት የቅርብ ድጋፍ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን እና ዋና ዋና ሥራዎችን በተግባራዊ ዕቅዱ መሰረት ለማስፈጸም ያላሰለሰ ጥረት ሲያደርጉ እንዲሁም የመጀመሪያ ሥራውን በብቃት ለመጀመርና ለሚመጣው ጊዜ ጠንካራ መሰረት ሲጥሉ ቆይተዋል። በዚህ ጊዜ ውስጥ የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት የሚከተሉትን ያካትታሉ።


- የተለያዩ ፖሊሲዎችን፣ አካሄዶችን፣ መመሪያዎችን እና ማኑዋሎችን ከባንኩ የረዥም ጊዜ ፍላጎት ጋር በማጣጣም ማጽደቅና ሥራ ላይ ማዋል፤
- የቢሮ ዕቃዎች የጨረታ ዶክመንቶችን በማዘጋጀትና በጨረታ ከሚመለከተው የቦርድ ንዑስ ኮሚቴ የቅርብ ድጋፍ ጋር ግዥ ማድረግ፤
- የዋና መ/ቤት እና የዐብይ ቅርንጫፍ ሕንጻ በመከራየት እና ለሥራ ዝግጁ ማድረግ፤
- ለሥራው በተዘጋጀው መመሪያ መሠረት ለየስራ መደቡ በተቀመጠው የሠራተኛ ቁጥር ቅጥር መፈጸም፤
- ቀልጣፋ እና ዘመናዊ የኮር ባንኪንግ ሲስተም እና የባንክ አፕሊኬሽኑን በብቃት ለማሳለጥ የሚያስችል የመረጃ ማዕከል ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ፤
- የተለያዩ የመደበኛ፣ ከወለድ ነጻ፣ ዲጂታል ባንኪንግ አገልግሎት እና ለሌሎች የባንክ አገልግሎቶችን ለመስጠት ሂደት መጀመር፤
- በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ቅርንጫፍ ማስፋፊያ ሊሆኑ የሚችሉ በታዎችን በመለየት የቅድመ ምዘና ማካሄድ፣ የቅርንጫፍ በታዎችን በመለየት፣ በመደራደር የኪራይ ውል መፈፀም፤
- ከብራንድ አማካሪዎች ጋር በመስራት ባንኩን በከፍተኛ ሁኔታ ለማስተዋወቅ እና የቅድመ እና ድህረ ብራንድ ሥራዎችን ማከናወን፤
- በሁሉም የሥራ መደቦች የሥራ መዘርዝር ላይ ተከታታይ ክለሳዎች መጀመር፤ በዕቅድ የተከናወኑ ተግባራት ጊዜያዊ መሻሻልን በሚመለከት ወቅታዊና ተገቢ አቅጣጫዎች እንዲሰጡ ለዳይሬክተሮች ቦርድ ወቅታዊ መረጃ መስጠት፤
- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለተለያዩ መደበኛና ከወለድ ነፃ የባንክ ሥራዎች ፈቃድ ለማግኘት የሚፈልገውን መስፈርት ማሟላትና ፈቃድ ማግኘት፣
- በተለያዩ ባንኮች የሚገኙትን የባለአክሲዮኖች መረጃ መሰብሰብና ማጠናከር፣ የዳይሬክተሮች ቦርድ ፕሮፋይሎችን ማዘጋጀት፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የመመሥረቻ ጽሁፍ ሰነድ ላይ እስካሁን ያልፈረሙ ባለአክሲዮኖች ፊርማ እንዲጀመር ማመልከቻ ማቅረብ፣
- የ2021/22 እና 2022/23 ዓመታዊ እቅድ ማዘጋጀት እና ትግበራውን መጀመር እና ሌሎችም።

## 2. ዋና ዋና የሥራ አፈፃፀም (ኦፐሬሽናል ፐርፎርማንስ)

### የተቀማጭ ገንዘብ ማሰባሰብ

የባንኮች ትርፋማነት ውጤታማ እና ቀልጣፋ የሀብት ማሰባሰብ ላይ የተመሰረተ ነው። በመሆኑም፣ የተሻሻሉ የሀብት ማሰባሰብ አቅምን ለማጎልበትና መሰረት ለመጣል ሁሉም ባለድርሻ አካላት ጥረትና ትኩረት ሰጥቶ የተቀማጭ ገንዘብ ማሰባሰብን ጨምሮ የተለያዩ ተግባራትን ማለትም አስፈላጊ የመረጃ ቴክኖሎጂዎችንና መሠረተ ልማቶችን በማጎልበት፣ ውጤታማና ቀልጣፋ ምርቶችን/አገልግሎቶችን በማቅረብ፣ ቅርንጫፎችን በማስፋፋት፣ ቀጣይነት ባለው መልኩ ሰፊ የማስተዋወቅና የምስል ግንባታ ስራዎችን በማከናወን፣ በየደረጃው በቂ፣ የሰለጠኑና እና ብቁ ባለሙያዎችን ማሰማራት እና ሌሎችም በዓመቱ የተቀማጭ ገንዘብ ለማሰባሰብ የሚረዱ ተግባራት እየተከናወኑ ይገኛሉ።

በእነዚህ ጥረቶች ምክንያት ባንኩ እ.ኤ.አ በ 2021/22 የሥራ ዘመን በጥቂት የሥራ ቀናት ውስጥ ብቻ አጠቃላይ የተቀማጭ ገንዘብ ብር 401.1 ሚሊዮን ማሰባሰብ ችሏል። ከዚህ የተቀማጭ ገንዘብ ውስጥ የአንበሳውን ድርሻ 93 በመቶ (ብር 372.6 ሚሊዮን) ከቁጠባ ሂሣብ ሲገኝ ቀሪው ደግሞ ከተንቀሳቃሽ ሂሳብ (ብር 28.5 ሚሊዮን, 7%) የተገኘ ነው።




### ደንበኛ

ባንኩ ሥራውን ከጀመረ ወዲህ ትልቁ ትኩረት ደንበኞችን ማዕከል ያደረገ ነው፣ ይህ ደግሞ ባንኩ የበለጠ ጥራት ያለው አገልግሎት ለደንበኞቹ እንዲሰጥ አግዞታል። በዚህም መሰረት ደንበኞችን የበለጠ ለመሳብ እና ለማቆየት እንዲሁም በገበያው ወይም በኢንዱስትሪው ውስጥ ብቁ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመቆየትና ትርፋማ ለመሆን በማቀድ ለደንበኞቹ አዳዲስ እና አስተማማኝ አገልግሎት ለማቅረብ የተለያዩ ሥራዎች ተሠርተዋል። ለምሳሌ፣ ተደራሽ ለመሆን በአጭር ጊዜ ብዙ ቅርንጫፎችን በተለያዩ የሀገራችን ክፍል በመክፈት አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርጓል፣ በሁሉም የመገናኛ መንገዶች ወይም ዘዴዎች ብዛት ያላቸው እና ሳቢ ማስታወቂያዎች ተሰራጭተዋል ወይም ተላልፈዋል፣ የተለያዩ የባንክ አገልግሎቶች ተጀምረዋል፣ በተጨማሪም የዲጂታል ባንኪንግ አገልግሎቶች በከፊል መጀመር የተከናወኑ ዋና ዋና ሥራዎች ናቸው። በመሆኑም በበጀት ዓመቱ ጥቂት ቀናት ውስጥ ብቻ 82,014 ደንበኞችን ማፍራት የተቻለ ሲሆን፣ ከእነዚህ ውስጥ 98 በመቶው ወይም 80,251 በቁጠባ ሒሳብ የተገኙ ሲሆን ቀሪዎቹ 728 እና 1,035 ደንበኞች ደግሞ በቅደም ተከተል በተንቀሳቃሽ ሒሳብ እና ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት የተከፈቱ ናቸው።

### ቅርንጫፍ

አንዱና ዋነኛው በባንኩ የስትራቴጂክ እቅድ ውስጥ የተቀመጠው እና እንደ ዋና እሴት የተያዘው በባንክ ተደራሽ ያልሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎችን እንዲሁም የባንክ ተጠቃሚ የሆኑ ማህበረሰቦችን ፍላጎት ለማርካት በብዙ አማራጮች ተደራሽነትን ማረጋገጥ ነው። ለዚህም ነው ባንኩ የምስረታ እለት ብቻ 72 ቅርንጫፎችን በመክፈት ወደ ሥራ የገባው። በመቀጠልም ባንኩ ተጨማሪ ሶስት ቅርንጫፎችን በመክፈት አጠቃላይ የቅርንጫፎቹን ቁጥር በበጀት አመቱ መጨረሻ ወደ 75 አድርሷል።

በተጨማሪም የቅርንጫፎች ብዛት ደንበኞችን በቅርበት ለማገልገል እና ተደራሽነትን ለማስፋት እንዲሁም ተቀማጭ ገንዘብ ለመሰብሰብ ከሚወስኑ ግብአቶች መካከል አንዱና አይተኬ ሚና ያለው በመሆኑ በቀጣይ ለሚከፈቱ ቅርንጫፎች የተለያዩ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ተሠርተዋል። ለዚህም ይረዳ ዘንድ በተለያዩ

የሀገሪቱ ክፍሎች ለቅርንጫፍ የሚሆኑ ቦታዎችን መገምገም እና መለየት፣ ለቅርንጫፎች የሚያስፈልጉትን ቁሳቁሶች ወይም ግብአቶችን ቀድሞ ማሟላት፣ በተመሳሳይይ መልኩ በቂ የሰው ሀይል ዝግጅት ማድረግ ይገኙበታል።

## 3. ገንዘብ ነክ (ፋይናንሽያል) አፈፃፀም

### ሀብት

እ.ኤ.አ ሰኔ 30 ቀን 2022 አጠቃላይ የባንኩ ሀብት ብር 7.1 ቢሊዮን የደረሰ ሲሆን ከጠቅላላ ሀብቱ ውስጥ በሌሎች ንግድ ባንኮች የተቀመጠው ገንዘብ 81 በመቶ ወይም ብር 5.7 ቢሊዮን ይዟል። የተቀረው ደግሞ በቋሚና ጊዜያዊ ንብረቶች የተያዘ ነው።


### የተከፈለ ካፒታል

ባንኩን ፈቃድ ተሰጥቶት የአክሲዮን ካፒታል ማሰባሰብ ከጀመረበት እ.ኤ.አ እስከ ሰኔ 30 2022 ድረስ ብር 4.8 ቢሊዮን የተከፈለ ካፒታል አከማችቷል። ሆኖም በበጀት ዓመቱ ጥቂት ቀናት ውስጥ ቃል ከተገባውና ካልተከፈለው እና የመመስረቻ ፅሁፉ እና በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ ተፈርሞ ሊገኝ ከሚችለው ምንም ተጨማሪ ካፒታል ማሰባሰብ አልተቻለም። ነገርግን በመተዳደሪያ ደንቡ እና በመመስረቻ ፅሁፉ ላይ ያልፈረሙ ባለአክሲዮኖች እንዲፈርሙ ቢፈቀድ ኖሮ የተከፈለ ካፒታል መጠን ከዚህ ከፍ ሊል ይችል ነበር። የባለአክሲዮኖች ቁጥር ከፍተኛ በመሆኑ ባንኩ የባለአክሲዮኖችን መረጃ በማጣራት እና በማጠናከር ላይም ከፍተኛ ተሳትፎ አድርጓል። በሌላ በኩል የባለአክሲዮኖች፣ የስብሰባ ቃለ ጉባኤ፣ የዳይሬክተሮች ቦርድ መግለጫ እና ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ለቀሪ ባለአክሲዮኖች ፊርማ ፈቃድ ለማግኘት ማመልከቻ ማቅረብ በሪፖርቱ ወቅት የተከናወኑ ሌሎች አበይት ጉዳዮች ነበሩ።

### ገቢ

በዋነኛነት ከአክሲዮን መመዝገቢያ ክፍያ በተሰበሰበው ከፍተኛ ገቢ ምክንያት የባንኩ ገቢ እ.ኤ.አ ሰኔ 30 2022 ብር 531 ሚሊዮን ደርሷል። በመሆኑም ከጠቅላላ ገቢው ውስጥ ሁለት ሦስተኛው የሚሆነው ከአገልግሎት ክፍያ (ብር 325.8 ሚሊዮን) የተገኘ ሲሆን ከሌሎች የንግድ ባንኮች የተሰበሰበው ወለድ ደግሞ ሁለተኛው ከፍተኛ ገቢ (ብር 182.1 ሚሊዮን) ነበር። በሌላ በኩል ባንኩ ከዲያስፖራ ባለአክሲዮኖች ከሰበሰበው የውጭ ምንዛሪ 22.5 ሚሊዮን ብር ገቢ አግኝቷል።


**እ.ኤ.አ እስከ ሰኔ 30 2022 ድረስ ያለ የገቢ ስርጭት**




### ወጪ

እ.ኤ.አ እስከ ሰኔ 30 2022 ድረስ ባንኩ አጠቃላይ ወጪው ብር 294 ሚሊዮን ደርሷል። ከጠቅላላ ወጪው ውስጥ ከፍተኛው ወጭ (174 ሚሊዮን ብር) የተከፈለው በዋናነት ሥራ ከመጀመሩ በፊት እና በኋላ ከማስታወቂያው ጋር በተያያዘ ወጪዎች፣ በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ኤጀንሲ ለባለአክሲዮኖች ለመመዝገቢያ የተደረገ ክፍያ እና ሌሎች አስተዳደራዊ ወጪዎች ነበር። ለሠራተኞች ደመወዝና ጥቅማጥቅም፣ የኢንቨስትመንት ንብረቶች የእርጅና ቅንስናሽ፣ የማይዳሰሱ ንብረቶችን የእርጅና ቅንስናሽ፣ እና ለአስቀማጮች የተከፈለ የወለድ ወጪ ቀሪውን ብር 101.6 ሚሊዮን፣ 12.7 ሚሊዮን ብር፣ 3.7 ሚሊዮን ብር፣ እና ብር 2.1 ሚሊዮን እንደ ቅደም ተከተላቸው ይይዛሉ።

**እ.ኤ.አ እስከ ሰኔ 30 2022 ድረስ ያለ የወጪ ስርጭት**




### ትርፍ

ከላይ በተጠቀሰው ገቢና ወጪ ምክንያት ባንኩ ከታክስ በፊት ብር 237 ሚሊዮን ጠቅላላ ትርፍ አስመዝግቧል። በዚህም መሰረት ብር 1000 ዋጋ ላለው የአንድ አክሲዮን ድርሻ ብር 40.80 መክፈል ያስችላል።

## 4. ገንዘብ ነክ ያልሆኑ ክንውኖች

### የሰው ሀብት ልማት

ባንኩ ተደራሽነቱንና የአገልግሎት አድማሱን ለማስፋት እንዲሁም ወደፊት ያቀዳቸውን ግቦች ለማሳካት አስፈላጊ ከሆኑ ነገሮች ውስጥ አንዱና ዋነኛው በሙያው የሰለጠነና ብቃት ያለው የሠራተኛ ሀይል ማሟላት ነው። ይህን ተግባራዊ ለማድረግ ይረዳ ዘንድ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ትክክለኛ ክህሎት ያላቸውና ሰፊ የባንክ ልምድ ያካበቱ እንዲሁም የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ የሚፈልገውን መስፈርት ያሟሉ ሠራተኞችን በመቅጠርና በፍጥነት ወደ ሥራ በማስገባት ለቀጣዩ ጊዜ ጠንካራ መሠረት እንዲይዝ ለማድረግ ያላሰለሰ ጥረት አድርገዋል።

በዚህም መሰረት እ.ኤ.አ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2022 ድረስ 1,408 ቋሚ እና 17 የኮንትራት ሠራተኞች ተቀጥረዋል። የሠራተኞች ስብጥርን ስንመለከት ከፍተኛ ቁጥር ያለው የሠራተኛው ክፍል (67 በመቶው) ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው ሲሆን ቀሪዎቹ (33 በመቶው) የድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ሲሆኑ ከእነዚህም ውስጥ አብዛኛዎቹ የጥበቃ ሠራተኞች ናቸው። በሌላ በኩል ባንኩ በአንድ ጊዜ ብዙ ቅርንጫፎችን በመክፈት (72 ቅርንጫፍ) ወደ ገበያው ስለተቀላቀለ ከጠቅላላው ሠራተኛ ወይም 88 በመቶ (1,249 ሠራተኞች) የተመደቡት በቅርንጫፍ ነው። ቀሪዎቹ ደግሞ በዋናው መሥሪያቤት በተለያዩ የሥራ ክፍሎች ተመድበዋል።

ልክ እንደ አዲስ ድርጅት ፈር ቀዳጅና እና በኢንዱስትሪው ውስጥ ካሉት ትላልቅ ተዋናዮች መካከል አንዱ ለመሆን እንደ መፈለጉ መጠን፣ ውጤታማ የሰው ሀብት ልማትን ማካሄድ እንደ ዋና የስትራቴጂ ግብ ተደርጎ ተወስዷል። ይህንን ተግባራዊ ለማድረግም የተለያዩ ተግባራት ተከናውነዋል፣ ለምሳሌ፣ የአቅም ማጎልበቻ እና የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች፣ የተለያዩ ፖሊሲዎችንና መመሪያዎችን በማዘጋጀት ወደ ሥራ ማስገባት፣ የፍላጎት ምዘና ማካሄድ፣ ለተለያየ ሥልጠና ሠልጣኞችን መለየት፣ የሥልጠና መርሃ ግብሮችን በተመደበው በጀት መሠረት ማዘጋጀት እና መወሰን እንዲሁም የተለያዩ ሥልጠናዎችን በውስጥ እና በውጫዊ አቅም መስጠት ከተከናወኑ ተግባራት መካከል ጥቂቶቹ ናቸው። በዚህም መሰረት እ.ኤ.አ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2022 ድረስ ባንኩ ለ1,277 ሠራተኞች በድምሩ 4.6 ሚሊዮን ብር ወጪ በማድረግ የተለያዩ የሥልጠና መርሃ ግብሮችን አከናውኗል። በተጨማሪም የሰው ሃይል አሠራር ሂደቶችን ከሰው ንክኪ ነፃ ለማድረግና እና በቴክኖሎጂ ለመቀየር ተከታታይነት ያለው የማሻሻያ ሥራዎች ተጀምረዋል፣ ይህም ውጤታማ እና ቀልጣፋ የመረጃ አሰባሰብ፣ የማከማቸት፣ የማሰራጨት እና የመተንተን ሂደትን ያካትታል።

### የመረጃ ቴክኖሎጂ

በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመታገዝ፣ ሰፊ፣ ተደራሽ፣ አስተማማኝ እና አዳዲስ የፋይናንስ እና የገንዘብ ነክ ያልሆኑ መፍትሄዎችን የሚመለከቱ የባንኩ አላማዎችን ከማሳካት አኳያ፣ሥራዎችን የሚያቃልል፣ የአሠራር ሂደቶችን የሚያቀላጥፍ፣ "በአፍሪካ ቀዳሚ እና ጨዋታ ቀያሪ ባንክ" ለመሆን በምናደርገው ሂደት ውስጥ

ደንበኞቻችንን ማስደሰት የሚያስችል ዘመናዊ አሠራር ቴክኖሎጂዎችን ለመተግበር፣ ባንኩ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። ስለሆነም ቴክኖሎጂ በተቋማችን ውስጥ በስፋት ጥቅም ላይ እየዋለ በሄደ ቁጥር፣ ውጤታማ፣ ቀልጣፋ እና የውድድር አቅምና እሴት ሊፈጥር የሚችል ዘመናዊ ቴክኖሎጂ መፈጠሩ አይቀሬ ነው።

በመሆኑም ባንኩ አገልግሎት አቅራቢ ከሆነው ተቋም (T24) እና ከአፈስፈፃሚው (USI) ጋር በመተባበር የመጀመሪያ ደረጃ ሥራውን (CBS) እንደ ሒሳብ መክፈት እና መሠረታዊ የደንበኞች ግብይት አገልግሎቶችን፣ ማስጀመር የሚያስችለውን ስርዓት (Retail Minimum Viable Products) ባንኩ በሩን ለደንበኞቹ ክፍት ከማድረጉ አስቀድሞ በተሳካ ሁኔታ አጠናቅቋል። እንደ ሪቴል ባንኪንግ ሲስተም፣ የፋይናንስ ስርአት እና ከወለድ ነፃ የባንኪንግ አገልግሎት ያሉ የተለያዩ ምርቶችን እና አገልግሎቶችን ማቀላጠፍ የሚጠይቁ የተለያዩ ወሳኝ ሞጁሎችን ዲዛይን ማድረግ እና መገንባት ሂደት በሚገባ ተጠናቆ ወደ ሥራ ገብቷል።

በተጨማሪም ባንኩ እንደ ብድር እና ንግድ አገልግሎቶች ያሉ ሌሎች ሞጁሎችን ማበልፀጉን ቀጥሏል። በሌላ በኩል የተለያዩ የባንኩን ሥራዎች በፍጥነት ለማስጀመር ያመቻ ዘንድ የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ሰርቨር (Primary and Secondary Server) ተዘጋጅቷል፣ በተጨማሪም ለሁሉም ቅርንጫፎች የኤፍቲፒ ሰርቨር (FTP server) ተዘጋጅቷል፣ እንዲሁም የችግር መከታተያ ስርዓቱ ተበጅቷል።

ከዚህም ሌላ ከጣቢያ-ወደ-ጣቢያ የቪፒኤን (VPN) ግንኙነትን ማረጋገጥና ከኢት-ስዊች፣ ከዳራ፣ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር ግንኙነትን፣ የኤስኤምኤስ ማስጀመሪያዎችን የማስተካከል እንዲሁም የመጀመርያው ምዕራፍ የአክሲዮን አስተዳደር ስርዓትን የማዘጋጀት ተግባራት ተከናውኗል።

የመረጃ ቋት ማዕከልን በተመለከተ፣ ባንኩ የራሱን ሕንጻ ገንብቶ የመረጃ ማዕከሉን በራሱ እስኪዘረጋ ድረስ፣ ሌላ አማራጭ መንገዶችን እንዲጠቀም ተወስኗል። በዚህም መሠረት ባንኩ የዳታ ሴንተር ኮሎኬሽን አገልግሎት ስምምነትን ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር የተፈራረመ ሲሆን፣ በመቀጠልም ባንኩ ሙሉ በሙሉ ወደ ሥራ ከመግባቱ አስቀድሞ የሁሉም የመሠረተ ልማት ግብዓቶች ዝርጋታና ተከላ ተጠናቅቆ ዝግጁ ሆኗል።

## ዲጂታል ባንኪንግ

አማራ ባንክ አሠራሩን ለማሳለጥ የተለያዩ ሥርዓቶችንና መሠረተ ልማቶችን ከመዘርጋት በተጨማሪ አማራጭ የዲጂታል የባንክ አገልግሎት አቅርቦትን ለማሳደግ የቴክኖሎጂ አቅምን በማጎልበት ላይ ይገኛል። ለዚህም የኤቲኤም ማሽኖችን በመጠቀም ተገልጋዩን ለማግኘት በሚደረገው ጥረት በአዲስ አበባ እና በባህር ዳር ከተማ የመጀመሪያ ስምንት ማሽኖችን በመትከልና ከኢት-ስዊች ጋር በማቀናጀት የሌሎች ባንኮች ካርዶችም ጥቅም ላይ እንዲውሉ ተደርጓል። በተመሳሳይ፣ የኤቲኤም ግብይት ሂደቶችን በማስጀመር ተጨማሪ የኤቲኤም እና POS ማሽኖች የግዥ ሂደት በጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛል። በኋላም ባንኩ የራሱን ካርድ በራሱ ማተም እስኪችል ድረስ፣ አማራጭ የካርድ ህትመት አገልግሎት ለማግኘት እንቅስቃሴ ሲደረግ ቆይቷል።

በሌላ በኩል የዲጂታል ባንኪንግ አገልግሎቶችን አቅርቦትና ተደራሽነት ለማሳደግ ብሎም የባንኩን ተወዳዳሪነት የሚያጎለብቱና በሀይ-ቴክ (hi-tech) እና በዲጂታል የታገዙ ፕላትፎርሞችን በመጠቀም እንደ ሞባይል፣ ኢንተርኔት እና የወኪል ባንክ አገልግሎቶችን በመዘርጋት የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ተከናውነዋል።

## የስጋት አስተዳደር

የባንኩን ስታራቴጂክ እቅድ ለማሳካት ከፍተኛ ሚና ካላቸው ሂደቶች ውስጥ የስጋት አያያዝ ዋነኛው መሆኑ ታውቆ፣ ለተሻለ የስጋት አያያዝ እና ተገዢነት ሥርዓት (Risk Management Process) መዘርጋት ባንኩ አስፈላጊውን ትኩረት ሰጥቶ ሲሠራ ቆይቷል።

የአማራ ባንክ እንደ አዲስ ጀማሪ ተቋም፣ ጤናማ እና ንቁ የስጋት አያያዝ ስርዓትን ለሚጠይቁና ከፍተኛ ችግር

ሊያመጡ ለሚችሉ በርካታ ስጋቶች ሊጋለጥ እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም ደህንነቱ የተጠበቀ እና ምቹ የንግድ አካባቢ መፍጠርን ከግምት ውስጥ በማስገባትና አስፈላጊውን ሁሉ ትኩረት በመስጠት፣ ራሱን የቻለና ከቁጥጥር መስፈርቶች ጋር በተጣጣመ የስጋት አስተዳደር መምሪያ ተቋቁሟል፡፡ መምሪያው በዋናነት ውጤታማ የስጋት አያያዝ ሥርዓትን ለመተግበር እና ለስጋት ምላሽ የሚሰጡ ውሳኔዎችን በማሳደግ፣ድንገተኛ ሥራዎችን እና ኪሳራዎችን በመቀነስ፣ በተቋማት ውስጥ ያሉ ስጋቶችን በመለየትና እርምጃ በመውሰድ እንዲሁም ለዘርፈ ብዙ ስጋቶች የሚሰጥ የትብብር ምላሽን በማጎልበት በተቋሙ ውስጥ የስጋት አያያዝ ባህልን ለማዳበር ሲሠራ ቆይቷል፡፡

ጠንካራ የስጋት አስተዳደር ፕሮግራምን (Risk Management Program) በማዘጋጀት እና በመተግበር መምሪያው በተቋቋመበት ጊዜ ሊከሰቱ የሚችሉ የረጅም ጊዜ ተፅእኖዎችን የሚፈጥሩ ስጋቶችን መለየት የጀመረ ሲሆን፣ ተያይዞም የባንኩን አሠራር ሊያደናቅፉ የሚችሉ ስጋቶችን በመለየትና የሚከላከሉ ሌሎች ዘዴዎችንም ሲጠቁም ቆይቷል፡፡ በሌላ በኩል፣ እያደገ የመጣውን አገራዊና ዓለም አቀፋዊ የቁጥጥር መስፈርቶችን ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ ውጤታማ ህጋዊ ያለሆነን ገንዘብ ህጋዊ አድርጎ ማቅረብና ለሽብርተኞች ፋይናንስ ድጋፍ ማድረግን (Anti-Money Laundering/Countering the Financing of Terrorism) መከላከል የሚያስችሉ ሥርአቶችን በመዘርጋት፣ ባንኩን ከገንዘብ እና ገንዘብ ነክ ካልሆኑ ኪሳራዎች ለመከላከል ክፍሉ ያላሰለሰ ጥረት አድርጓል፡፡

## ማኅበራዊ ኃላፊነት

በባንኩ ስትራቴጂክ ዓላማ ውስጥ በግልፅ እንደተመለከተው ባንኩን በተግባር ከባንክ ባሻገር ለማድረግና የተለያዩ ማኅበራዊ ኃላፊነቶችን በተገቢው መንገድ ለመወጣት፣ በዓመቱ ውስጥ ባሉት ጥቂት የሥራ ቀናት ለተለያዩ የኮርፖሬት ማኅበራዊ ኃላፊነት ተግባራት እና እንቅስቃሴዎች ተገቢውን ትኩረትና በጀት መድቧል፡፡

ባንኩ በይፋ አገልግሎት መስጠት የጀመረበትን ዕለት ምክንያት በማድረግ በአዲስ አበባ ከተማ ላሉ ተጓዦች በሙሉ የአንበሳ የከተማ አውቶብስ ትኬቶችን ስፖንሰር በማድረግ እና በዕለቱ በተመረጡ ሆስፒታሎች ለተወለዱ ህጻናት ስጦታ በመስጠት፣ እንዲሁም በተለያዩ አካባቢዎች ችግኝ በመትከል እና የባንኩ ሠራተኞችን በማደራጀት በተለያዩ ክልሎች ደም እንዲለግሱ በማድረግ ባንኩ ማኅበራዊ ኃላፊነቱን በተግባር እየተወጣ መሆኑን ካሳየባቸው ተግባራት መካከል ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

ባንኩ ከህብረተሰቡ ጋር ዘላቂነት ያለውና የማይናወጥ አጋርነት ለመፍጠር ያለውን የረዥም ጊዜ ፍላጎት ተከትሎ፣ ወደፊት ከማህበረሰቡ ጋር ያለውን ሁለንተናዊ ትስስር ለማሳካት የታቀዱ ሁሉንም ውጥኖች በጥራት ለመንደፍ፣ ለመተግበር እና ለመከታተል ያስችለው ዘንድ ባንኩ በቀጣይ ጊዜያት ትኩረት ሊሰጣቸው ስለሚገባ ሥራዎች ጥልቅ ግምገማ አካሂዷል፡፡

## ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች

የአማራ ባንክ የኢትዮጵያን የባንክ ኢንደስትሪን የተቀላቀለው ገበያው በከፍተኛ የፖሊሲ ለውጥና እና ብዙ ተዋናዮች ተሳትፎ ማድረግ በጀመሩበት ወቅት ነው፡፡ የውጭ ባንኮች እንዲገቡ መንገድ የሚከፍት የፖሊሲ ለውጥ፤ የካፒታል ገበያ መመስረት፤ እንደ ሳፋሪኮም ካሉ የውጭ የቴሌኮም ኦፕሬተሮች ጨምሮ ቴሌኮም በፋይናንሺያል አገልግሎት አቅርቦት ላይ እንዲሠሩ የመፍቀድ እና ሌሎች እምቅ አቅም ያላቸው የፊንቴክ አዳዲስ ገቢዎች ኢንዱስትሪውን ወደ አዲስ ምዕራፍ እያሸጋገረው ነው፡፡ ልማቱ እድሎችም ተግዳሮቶችም ይዞ እስከመጣ ድረስ የአማራ ባንክ ተግዳሮቶችን ለማሸነፍና ዕድሎችን ለመጠቀም በንቃት ምላሽ መስጠት ይኖርበታል፡፡ ለዚህም ባንኩ የአይቲ፣ የዲጂታል እና የሰው ሃብትን ጨምሮ የተለያዩ ቁልፍ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል፡፡ ይህ ተግባር አማራ ባንክን በሚቀጥለው የበጀት ዓመት በተለዋዋጭ ሁኔታዎች ውስጥ ያለችግር እንዲጓዝ ያግዘዋል፡፡

በኢንዱስትሪው ውስጥ የሚፈጠሩ አዳዲስና ፈጣን ለውጦችን ወይም በአለምአቀፍ እና በአገር አቀፍ ደረጃ የሚከናወኑ ለውጦችን ምላሽ ለመስጠት የባንኩ አስተዳደር እና የዳይሬክተሮች ቦርድ የባንኩን ስትራቴጂ

መገምገም አስፈላጊ ሆኖ አግኝተውታል። ይህንንም ስራ ለማከናወን ታዋቂ አለም አቀፍ አማካሪ ድርጅት የሚቀጠር ይሆናል።

በባንክ ኢንዱስትሪ ውስጥ ጥሩ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመቆየት እና ልዩነትን ለመፍጠር ዘመናዊ ቴክኖሎጂን እና ዲጂታል ልህቀትን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ይህም የባንካችን ቁልፍ የትኩረት አቅጣጫ ይሆናል። ባንኩ ሥራዎችን የበለጠ ውጤታማ እና ቀልጣፋ ለማድረግ የዲጂታል አቅርቦቶችን በማመቻቸት ደንበኞቹን ተደራሽ ለማድረግ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀምን የበለጠ ያሚያስፋፋ ይሆናል። ይህም ባንኩ ሰፊ የክፍያ መፍትሄዎችን በመጠቀም አዳዲስ እድሎችን እንዲያገኝ በመርዳት እና ደንበኞቻችን ቀላል፣ ፈጣን እና ደኅንነቱ በተጠበቀ መንገድ ግብይቶችን እንዲያደርጉ በማድረግ ረገድ ትልቅ ሚና ይጫወታል።

በተጨማሪም ባንኩ ለሁሉም ባለድርሻ አካላት ቀጣይነት ያለው የወደፊት የመፈፀም አቅም ለመገንባት እና የአሠራር ብቃትን ለማሳደግ በሚደረገው ጥረት የሁሉንም ፍላጎቶ ተግባራዊ ለማድረግ በትብብር ይሠራል።

ከባንኩ የትኩረት አቅጣጫዎች የተወሰኑት የሚከተሉት ናቸው፡- ቅርንጫፍ በማስፋትና እና በዲጂታል ቻናሎች ተደራሽነቱን ማጠናከር፤ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ፍላጎት ሊያሟሉ የሚችሉ ሰፊ የአገልግሎት አማራጮችን ተደራሽ ማድረግ፤ በሠራተኞቻችን መካከል ከፍተኛ የአፈፃፀም ባህልን ማዳበር እና ነገን ዝግጁ ለማድረግ በሰው ሀብት ልማት ላይ ኢንቨስት ማድረግ፤ ችሎታ ያለው እና ሥራ ወዳድ የሰው ኃይል ማፍራት፤ አስተማማኝ እና ምቹ የአገልግሎት ጥራትን ዝግጁ ማድረግ፤ የደንበኞች አገልግሎት ግንኙነቶችን ማሳደግ፤ የሀብት ማሰባሰብ እና የመጠቀም አቅምን ማሳደግ፤ የበለጠ ስልጡን ድርጅት መመስረት፤ የላቀ የአሠራር ሂደት ውጤታማነትን ማጎልበት እና ጥሩ የድርጅት ስምና ባህልን መገንባት፤ማሳደግ መጠበቅ ናቸው።

በተመሳሳይ የአማራ ባንክ "ከባንክ ባሻገር" የሚለውን መርሁን እውን ለማድረግ በከፍተኛ ቁርጠኝነት ይሠራል። የአማራ ባንክ በህዝብ የተመሰረተ የማህበረሰብ ባንክ እንደመሆኑ መጠን ከግለሰብ እስከ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ ድረስ ድጋፍ ለማድረግ እና ከህብረተሰቡ ጋር የረዥም ጊዜ ግንኙነት ለመፍጠር የተለያዩ የማኅበራዊ ኃላፊነት ሥራዎችን ለመሥራትና ለህብረተሰቡ ደኅንነት የበኩሉን አስተዋጽኦ ለማበርከት ቁርጠኛ ነው።

እስካሁን ባለው ውጤት ላይ በመመሥረት፣ በእንደሰትሪው ውስጥ ያለውን ተለዋዋጭ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ የአማራ ባንክ "ከባንክ ባሻገር" በሚለው መርህ ላይ የገባውን ቃል አክብሮ በባንክ ዘርፍ ላይ ለውጥ በማምጣት "ከአፍሪካ ቀዳሚ እና ጨዋታ ቀያሪ ባንክ" የመሆን ርዕዩን እውን ያደርጋል።

# የውጪ ኦዲተሮች ሪፖርት

TMS Plus

Tafesse,Shisema and Ayalew Certified Audit Partnership
Chartered Certified Accountants (UK) and Authorised Auditors (Ethiopia)
Member Firm of HLB International
THE GLOBAL ADVISORY AND ACCOUNTING NETWORK

HLB Ethiopia

Tel. 251-011-8961752 /011 6180638 Mob. 0911 229425 /0930 034356/0930 034357 Fax: 251-011 662 12 70/60
E-mail:- tafessef@gmail.com / tafessef@hotmail.com P.O.Box 110690 Addis Ababa - Ethiopia

## የአማራ ባንክ አክሲዮን ማህበር እ.ኤ.አ. ከፌብርዋሪ 11 እስከ ጁን 30/2022 በተዘጋጀው ሂሳብ ላይ የቀረበ

## የውጭ ኦዲተሮች ሪፖርት

## በሂሳብ መግለጫዎች ኦዲት ላይ የቀረበ ሪፖርት
## የሙያ አስተያየት

ከዚህ ሪፖርት ጋር ተያይዘው የቀረቡትንና እ.አ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ ጁን 30/2022 (በእኛ አቆጣጠር ከየካቲት 4 እስከ ሰኔ 23 ቀን 2014 ዓ.ም) ለነበረው ጊዜ የተዘጋጁትን የአማራ ባንክ አክሲዮን ማህበር የሀብትና ዕዳ መግለጫ፤ የትርፍና ኪሳራ እና ሌሎች ጠቅላላ ገቢዎች መግለጫ፤ በተጣራ ሃብት ላይ የታየ ለውጥ መግለጫ ፤ የጥሬ ገንዘብ ፍሰት መግለጫ እንዲሁም ኩባንያው የሚከተላቸውን የሂሳብ አሰራር ፖሊሲዎች እና ማብራሪያዎች ያካተቱትን የሂሳብ መግለጫዎች ኦዲት አድርገናል፡፡

በእኛ አስተያየት ከዚህ ሪፖርት ጋር ተያይዘው የቀረቡት የሂሳብ መግለጫዎችና አባሪዎቻቸው አለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎችን (IFRS) ተከትለው የተዘጋጁ ሲሆኑ በአጠቃላይ አክሲዮን ማህበሩ እ.አ.አ ጁን 30/ 2022 የነበረውን ሀብትና ዕዳ እንዲሁም ከላይ በተጠቀሰው ጊዜ የነበረውን የሂሳብ እንቅስቃሴ እና የጥሬ ገንዘብ ፍሰት በሚገባ ያሳያሉ፡፡

## የአስተያየታችን መሰረት

የኦዲት ስራችንን ያከናወንነው አለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን በመከተል ሲሆን በእነዚህ ደረጃዎች መሰረት የሚጠበቅብን ኃላፊነት ከዚህ በታች የኦዲተሮች ሃላፊነት በሚለው ርዕስ ስር ተመልክቷል፡፡ የአለም አቀፍ የሂሳብ ባለሙያዎች የስነምግባር ደረጃዎች ቦርድ ለሂሳብ ባለሙያዎች ያወጣው የስነ-ምግባር ኮድ በሚጠይቀው እና በኢትዮጵያ ውስጥ ለተካሄደው ኦዲት አስፈላጊ በሆኑት የስነምግባር መርሆዎች መሰረት ከአክሲዮን ማህበሩ ነጻ እና ገለልተኛ ሆነን ስራችንን አከናውነናል፡፡ እንዲሁም የስነምግባር ደንቡ የሚጠይቃቸውን እና የሚጠበቁብንን ሌሎች ኃላፊነቶች አሟልተናል፡፡

ከዚህ በላይ የሰጠነው የሙያ አስተያየት ደረጃውን ተከትለን ባከናወንነው የኦዲት ስራና በቀረበልን የኦዲት ማስረጃ በመተማመን ነው፡፡

## የሂሳብ መግለጫዎችን በተመለከተ የዳሬክተሮች ቦርድ ኃላፊነት

አለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎችን በመከተል የሂሳብ መግለጫዎችን አዘጋጅቶ ማቅረብ እንዲሁም ሆን ተብሎም ሆነ ወይንም በስህተት ከሚፈፀም ጉልህ ስህተት ነፃ የሆኑ የሂሳብ መግለጫዎችን ለማዘጋጀት አስፈላጊ ናቸው ብሎ ያመነባቸውን የውስጥ ቁጥጥር ስርዓቶች መዘርጋት የባንኩ የዳሬክተሮች ቦርድ ኃላፊነት ነው፡፡ ቦርዱ የሂሳብ መግለጫዎችን በሚያዘጋጅበት ወቅት የኩባንያውን ቀጣይነት በመገምገም ስጋት የሚፈጥሩ ሁኔታዎችን በግልፅ ማመላከትና የኩባንያውን መፍረስ ወይም የአንዳንድ ኦፕሬሽኖችን ስራ ማቆም የሚያስገድዱ ሁኔታዎች ካላጋጠሙ በስተቀር የኩባንያውን ቀጣይነት በማሰብ ሂሳቡ የተዘጋጀ መሆኑን የመግለፅ ኃላፊነት አለበት፡፡

የዳይሬክተሮች ቦርድ የኩባንያውን የፋይናንሻል ሪፖርት ሂደት የመከታተል ተጨማሪ ኃላፊነት አለበት ።

## የኦዲተሮች ኃላፊነት

የእኛ ኃላፊነት የቀረቡት የሂሳብ መግለጫዎች ሆን ተብሎም ሆነ በስህተት ከሚፈፀም ጉልህ ስህተት ነፃ ስለመሆናቸው ምክንያታዊ ማረጋገጫ መስጠትና ይህንኑ አስተያየታችንን በሪፖርታችን መግለፅ ነው። ምክንያታዊ የሆነ ማረጋገጫ ለመስጠት የሚከናወነው ተግባር በሂሳቡ ውስጥ ሊኖሩ የሚችሉ ጉልህ ስህተቶችን በሙሉ ፈልጎ ያገኛል ተብሎ አይጠበቅም። ምክንያቱም ምክንያታዊ ማረጋገጫ በከፍተኛ ደረጃ የሚታይ የማረጋገጥ ሂደት በመሆኑ አለም አቀፍ የኦዲት ደረዳዎችን በመከተል የሚከናወነው ኦዲትም ቢሆን ጉልህ ስህተቶችን ሁልጊዜ ፈልጎ የማግኘት ዋስትና ስለማይሰጥ ነው። ስህተቶች ሆን ተብሎ ወይንም በስህተት የሚፈጸሙና በተናጠል ወይም በድምር ጉልህ ሆነው የሂሳብ መግለጫዎችን መሰረት አድርጎ በሚወሰን ኢኮኖሚያዊ ውሳኔ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ።

## የሌሎች ህጋዊ ሁኔታዎች ኦዲት ሪፖርት

በ 2013 ዓ.ም በወጣው የኢትዮጵያ ንግድ ህግ አዋጅ 1243/2021 በሚያዘው መሰረት የቀረበው የዳሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት ላይ የሂሳብ መግለጫዎቹን በተመለከተ ከቀረበው ሪፖርት የተለየ አስተያየት የሌለን መሆኑን እየገለጽን ጠቅላላ ጉባኤው የዳሬክተሮቹን ሪፖርት እንዲያፀድቀው አስተያየታችንን እንሰጣለን።

Taf Shi CAy

TMS Plus — Tafesse, Shisema & Ayalew — Certified Audit Partnership

*ታፈሰ፣ ሺሰማ እና አያሌው የኦዲት አገልግሎት የህብረት ሽርክና ማኅበር*
*የተመሰከረላቸው የሂሳብ አዋቂዎች(ዩኬ)*
*የተፈቀደላቸው ኦዲተሮች (ኢትዮጵያ)*
*የአማራ ባንክ አክስዮን ማህበር የውጭ ኦዲተሮች*

*አዲስ አበባ*
*ጥቅምት 16 ቀን 2015 ዓ.ም*

**አማራ ባንክ አክሲዮን ማህበር**

የትርፍ ወይም ኪሳራ እና አጠቃላይ ገቢ መግለጫ

ከየካቲት 4 ቀን 2014 እስከ ሰኔ 23 ቀን 2014 ባለው ጊዜ ውስጥ

| | ማብራሪያ | ሰኔ 23 ቀን 2014 ብር'000 |
|---|---|---|
| ከወለድ የተገኘ ገቢ | 5 | 182,143 |
| የወለድ ወጪ | 6 | (2,058) |
| **የተጣራ የወለድ ገቢ** | | **180,086** |
| ከአገልግሎት እና ከኮሚሽን | 7 | 348,860 |
| **ጠቅላላ የአገልግሎት ገቢ** | | **528,945** |
| የሰራተኛ ወጪዎች | 8 | (101,597) |
| ህልዎታዊ ግዝፈት ለሌላቸው የተደረገ ቅናሽ | 14 | (3,686) |
| ከቋሚ ንብረት የተደረገ የዕርጅና ቅናሽ | 15 | (12,735) |
| ለሌሎች መደበኛ ወጪዎች | 9 | (173,963) |
| | | **(291,981)** |
| **ትርፍ ከግብር በፊት** | | **236,964** |
| የግብር ወጪ | 10,a | (39,853) |
| **ትርፍ ከግብር በኋላ** | | **197,111** |
| **ተጨማሪ ገቢዎች ተገቢው የግብር ዕዳ ከተቀነሰ በኋላ** | | |
| **በቀጣይ ወደ ትርፍ እና ኪሳራ መግለጫ የማይዞሩ** | | |
| በሰራተኞች ጥቅማ ጥቅም ላይ በተሰላ የድጋሚ ልኬት የተገኘ ገቢ ወይም ወጪ | | - |
| በድጋሚ ልኬቱ ላይ የተገኘ የዘገየ የታክስ ሃብት ወይም ዕዳ | | - |
| በባንኩ ኢንቨስትመንቶች ላይ በተሰላ የገበያ ዋጋ የተገኘ ገቢ ወይም ወጪ | | - |
| በገበያ ዋጋ ላይ የተገኘ የዘገየ የታክስ ሃብት ወይም ዕዳ | | - |
| | | - |
| **የዓመቱ አጠቃላይ የተጣራ ገቢ** | | **197,111** |
| ባለአክሲዮኖች በአንድ አክሲዮን የሚያገኙት ትርፍ | 19 | 0.04 |

## አማራ ባንክ አክሲዮን ማህበር

የሃብት እና ዕዳ መግለጫ

ሰኔ 23 ቀን 2014 ለተጠናቀቀው በጀት ዓመት

| | ማብራሪያ | ሰኔ 23 ቀን 2014 ብር'000 |
|---|---|---|
| **ሃብት** | | |
| በእጅ ያለ ገንዘብ እና በባንክ ያለ ተቀማጭ | 11 | 5,919,179 |
| ኢንቨስትመንት | | |
| - የገበያ ዋጋ ልኬቱ በተጨማሪ የሆነ የሆነ ኢንቨስትመንት | 12 | 10,222 |
| ለሌሎች ሃብቶች | 13 | 87,750 |
| ህልወታዊ ግዝፈት የሌላቸው ንብረቶች | 14 | 58,963 |
| ቋሚ ንብረት | 15 | 477,484 |
| ሀብት የመጠቀም መብት | 16 | 519,642 |
| **ጠቅላላ ሃብት** | | **7,073,240** |
| **ዕዳ** | | |
| የደንበኞች ተቀማጭ ገንዘብ | 17 | 401,097 |
| የግብር ዕዳ | 10,c | 18,478 |
| ሌሎች ዕዳዎች | 18 | 1,603,537 |
| ወደፊት የሚከፈል የግብር ዕዳ | 10,e | 21,375 |
| **ጠቅላላ ዕዳ** | | **2,044,487** |
| **ካፒታል እና መጠባበቂያ** | | |
| የተከፈለ ካፒታል | 19 | 4,831,642 |
| ያልተከፋፈለ ትርፍ | 20 | 147,833 |
| ህጋዊ የመጠባበቂያ ሂሳብ | 21 | 49,278 |
| **ጠቅላላ ካፒታል** | | **5,028,753** |
| **ጠቅላላ ዕዳ እና ካፒታል** | | **7,073,240** |

**መላኩ ፈንታ**
**የቦርድ ሊቀመንበር**

**ሄኖክ ከበደ**
**ዋና ስራ አስፈፃሚ**

## አማራ ባንክ አክሲዮን ማህበር

በአክሲዮን ማህበሩ ካፒታል ላይ የታየውን ለውጥ የሚያሳይ መግለጫ

ከየካቲት 4 ቀን 2014 እስከ ሰኔ 23 ቀን 2014 ባለው ጊዜ ውስጥ

| | ማብራሪያ | የተከፈለ የካፒታል ብር '000 | ያልተከፋፈለ ትርፍ ብር '000 | ሌሎች መጠባበቂያ ብር '000 | ሕጋዊ መጠባበቂያ ብር '000 | የተቆጣጠሪ አካል የስጋት መጠባበቂያ ብር '000 | ለልዩ መጠባበቂያ ብር '000 | ድምር ብር '000 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **የካቲት 4 ቀን 2014 የታየ** | | 4,825,764 | | | | | | 4,825,764 |
| ከአክሲዮኖች ሽያጭ የተሰበሰበ | | 5,878 | | | | | | 5,878 |
| በአመቱ የተገኘ ትርፍ | | | 197,111 | | | | | 197,111 |
| ወደ ህጋዊ መጠባበቂያ የዞረ | 21 | | (49,278) | | 49,278 | | | - |
| **ሰኔ 23 ቀን 2014 ላይ የታየ** | | **4,831,642** | **147,833** | **-** | **49,278** | **-** | **-** | **5,028,753** |
| **ጠቅላላ ከፒታልና መጠባበቂያ ሂሳቦች** | | | | | | | | |

## አማራ ባንክ አክሲዮን ማህበር

የጥሬ ገንዘብ ፍሰት መግለጫ

ከየካቲት 4 ቀን 2014 እስከ ሰኔ 23 ቀን 2014 ባለው ጊዜ ውስጥ

| | ማብራሪያ | ሰኔ 23 ቀን 2014 ብር'000 |
|---|---|---|
| **ከመደበኛ ስራ እንቅስቃሴ የተገኘ የተጣራ ገንዘብ** | | |
| ከመደበኛ ስራ እንቅስቃሴ የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ፍሰት | 22 | 2,170,269 |
| ከመደበኛ ስራ እንቅስቃሴ የተገኘ የተጣራ ገንዘብ ገቢ | | 2,170,269 |
| **ለ ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ የወጣ** | | |
| የአክሲዮን ግዢ ኢንቨስትመንት | 12 | (10,222) |
| ግዝፋዊ ህልዎት ለሌላቸው ሃብቶች የተከፈለ | 14 | (62,648) |
| የቋሚ እቃዎች ግዢ | 15 | (490,219) |
| ለሊዝ የተከፈለ | | (519,642) |
| **ከኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ላይ የተጣራ ወጪ** | | **(1,082,732)** |
| **ከፋይናንስ እንቅስቃሴ** | | |
| የተሸጡ አክሲዮኖች | 19 | 4,831,642 |
| **ከ ፋይናንስ እንቅስቃሴ የተገኘ የተጣራ ገንዘብ** | | 4,831,642 |
| የአመቱ የተጣራ የጥሬ ገንዘብ ጭማሪ | | 5,919,179 |
| **በዓመቱ መጨረሻ ላይ የታየ የጥሬ ገንዘብ መጠን** | 11 | **5,919,179** |